## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

# የውሃ ቆጣሪ ንባብ ሥራ የአሠራር መመሪያ ቁጥር 9/2012

## መግቢያ

ባለስልጣኑ ለእያንዳንዱ የውሃ አገልግሎት ደንበኛ በውል የውሃ ቆጣሪ በመግጠም የደንበኞችን አጠቃቀም በየወሩ በሚወሰድ ንባብ እና በባለስልጣኑ የውሃ ሽያጭ ታሪፍ መሠረት የየወሩን የአገልግሎት ክፍያ የሚሰበስብ ሲሆን ይህም ባለስልጣኑ በአዋጅ ተፈቅዶለት ከሚሰበስባቸው ገቢዎች ዋንኛው እና  በቀጥታ በውሃ ቆጣሪ ንባብ ጥራት ላይ መሠረት ያደረገ በመሆኑ፡፡

የውሃ ቆጣሪ ንባብ ላይ የሚከሰቱት ችግሮች ደንበኞች ያልተጠቀሙበትን ከፍተኛ የውሃ ዋጋ እንዲጠየቁ የማድረግ ፣ የደንበኞች ቆጣሪ በወቅቱ ሳይነበብ በመቅረቱ ለተራዘመ ጊዜ የቆጣሪ ግብር ብቻ የሚጠየቁ እና ደንበኞች አጠቃቀም ከፍተኛ የታሪፍ ምድብ ውስጥ መግባት አላግባብ ከፍተኛ ክፍያ እንዲከፍሉ የማድረጉ፣ አዲስ የውሃ ቆጣሪ የተገጠመላቸውን ደንበኞች የመጀመሪያ ንባብ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አለመነበቡ ደንበኞች የፍጆታ ሂሳባቸውን በወቅቱ ለመክፈል እንዳይችሉ በማድረጉ እና ደንበኞች በየወሩ አንባቢው ያነበበውን ንባብ በንባብ ካርድ ላይ ባለመጻፉ ትክክለኛ ንባብ ስለመወሰዱ ለማረጋገጥ ባለመቻላቸው በቆጣሪ ንባብ ስራ ላይ የግልፅነትና ተጠያቂነት እንዳይኖር እንቅፋት በመፍጠሩ ባለስልጣኑ ይህን ዋነኛ ገቢውን በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ከማድረጉም በላይ በደንበኞች ላይ የመልካም አስተዳደር ችግር እየፈጠረ በመሆኑ፡፡

ይህንን የውሃ ቆጣሪ ንባብ ተግባር ችግር በመቅረፍ የንባብ ስራውን በጥራትና ተጠያቂነት በሰፈነበት ሁኔታ ለማከናወን የሚረዳ እና የደንበኞች የውሃ አገልግሎት ሂሳብ ክፍያን ከቅሬታ የፀዳ እንዲሁም የደንበኞችን እርካታ ባረጋገጠ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያስችል እና ባለስልጣኑ ዋነኛ ገቢውን በጥራት እና በብቃት ለመሰብሰብ የሚያስችል አሰራር መኖር ያለበት መሆኑ በመታመኑ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀፅ 1

### አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ውኃና ፍሳሽ ባለሥልጣን የውሃ ቆጣሪ ንባብ ሥራ የአሠራር መመሪያ ቁጥር 9/2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል።››

### አንቀፅ 2

### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1. ‹‹ **ባለስልጣን**›› ማለት የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን ነው።
2. ‹‹**ዋና ሥራ አስኪያጅ**›› ማለት የባለስልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው።
3. ‹‹ **የውሃ ዘርፍ**›› ማለት የውሃ አቅርቦትና ስርጭት ም/ ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው።
4. ‹‹ **ቅርንጫፍ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ ቤት**›› ማለት እንደ ቃሉ አግባብ በባለስልጣኑ ስር ያሉ ቅርንጫፍ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ ቤቶች ማለት ነው።
5. ‹‹ **ደንበኛ**›› ማለት ከባለስልጣኑ ጋር ውል ገብቶ የውሃ መስመር ቅጥያ የተሰጠው የባለስልጣኑ የውሃ አገልግሎት ተጠቃሚ ነው።
6. ‹‹ **ቆጣሪ አንባቢ**›› ማለት የውሃ ቅጥያ ያላቸው ደንበኞችን የውሃ ቆጣሪ በየወሩ ቤት ለቤት በመሄድ የውሃ ቆጣሪ ንባቡን የሚመዘግብ ሰው ማለት ነው።
7. ‹‹ **የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ**›› ማለት የቆጣሪ አንባቢዎችን ሥራ የሚቆጣጠር ፣ የሚደግፍ እና የሚያስተባበር ሰው ማለት ነው።
8. ‹‹ **የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ**›› በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የየጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ እና በስሩ የተዋቀሩ በክ/ ከተማ ወይም በወረዳ ያሉ ጽ/ ቤቶች ማለት ነው።

9. ‹‹ **የቆጣሪ አንባቢ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር**›› ማለት የውሃ ቆጣሪ አንባቢዎችን በመጠቀም የውሃ ቆጣሪ ንባብ ሥራን ለመሥራት ከቅርንጫፍ ጽ/ ቤቶች ጋር ውል የገባ ኢንተርፕራይዝ ወይም ማህበር ነው፡፡

10. ‹‹ **የማንበቢያ መጽሃፍ**›› ማለት ቆጣሪ አንባቢዎች የንባብ ሥራን ለማከናወን ከቅርንጫፍ ጽ/ ቤቶች የሚረከቡት የደንበኞችን አድራሻ እና የውል ቁጥር የያዘ የውሃ ቆጣሪ ንባብ የሚመዘገብበት መፅሃፍ ነው፡፡

11. ‹‹ **የማንበቢያ ካርድ**›› ማለት በደንበኞች ቤት የሚቀመጥ ቆጣሪ አንባቢ በማንበቢያ መጽሃፍ ላይ የመዘገበውን የቆጣሪ ንባብ ፣ ንባቡ የተወሰደበትን ቀን እና ሰዓት መዝግቦ ስለትክክለኛነቱ በፊርማ የሚያረጋግጥበት ካርድ ነው፡፡

12. ‹‹**አኖማሊስ**›› ማለት የቆጣሪ ንባብ ወደ ኮምፒተር ከተመዘገበ በኃላ ከባለፈው ወር አጠቃቀም አንጻር ሲነጻጸር ምንም ያልተጠቀመ (Zero Consumption) ወይም ከመጨረሻ የተመዘገበ ንባብ ያነሰ ንባብ (Over Charge) ወይም ከፍተኛ አጠቃቀም (Increased Consumption) ወይም የቀነሰ ፍጆታ (Decreased Consumption) ማለት ነው፡፡

## አንቀፅ 3
## የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማንኛውም ደረጃ ላይ ባሉ የባለስልጣኑ የሥራ መሪዎች፣ ሠራተኞች ፣የቆጣሪ ንባብ አስተባባሪዎች ፣የቆጣሪ ንባብ ፣ ቢል ዝግጅትና ሽያጭ ኬዝ ቲም መሪዎች፣የውሃ ቆጣሪ ንባብ እና የውሃ ቆጣሪ ንባብ ቁጥጥር ተግባራትን በሚፈጽሙ የ 3ኛ ወገን የውሃ ቆጣሪ አንባቢ ማህበራት (ወይም ኢንተርፕራይዞች) ፣ የማህበራቱ አባላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ተግባርና ኃላፊነት

## አንቀፅ 4

## የቅርንጫፍ ጽ/ ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

1. የቆጣሪ ንባብ ሥራ የሚሠሩ ማህበራትን ይመለምላል ይቀጥራል፡፡
2. የቆጣሪ አንባቢ ማህበራት እና አባላት በደንበኞች ቤት ለውሃ ቆጣሪ ንባብ ሥራ ሲሰማሩ የደንበኞችን ደህንነት ለማረጋገጥ ሲባል ህጋዊ ዋስትና እንዲያስይዙ ያደርጋል፡፡
3. ለቆጣሪ አንባቢዎች በሥራ ላይ ሲሰማሩ ህጋዊነታቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ይሰጣል፡፡

4. ለቆጣሪ አንባቢዎች የቆጣሪ ንባብ የተግባር አፈጻጸምን በተመለከተ እና አንባቢዎች ሊኖራቸው ስለሚገባ ስነምግባር ስልጠና ይሠጣል ፡፡
5. አዲስ ቅጥያ ያገኙ ደንበኞችን በማንበቢያ መጽሃፍ ላይ መመዝገብ ለቆጣሪ አንባቢ ማህበራት አስፈርሞ ያስረክባል፡፡
6. የቆጣሪ አንባቢዎች በደንበኞች ቤት የሚያስቀምጧቸው ደረጃቸውን የጠበቁ የማንበቢያ ካርዶችን ያዘጋጃል፣
7. የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪዎችን ይመድባል ፡፡
8. የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪና የደንበኞችን ወይም ቆጣሪ አንባቢ ጥመርታን ይወስናል፡፡
9. አንድ የቆጣሪ አንባቢ በወር የሚያነበውን የቆጣሪ ብዛት በቆጣሪ ንባብ ጥራት እና በደንበኞች እርካታ ላይ መሠረት አድርጎ ይወስናል እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው የቆጣሪ አንባቢና ደንበኛ ጥመርታን ይከልሳል፡፡
10. የቆጣሪ አንባዎች ከቆጣሪ ንባብ ጎን ለጎን መሠራት ያለባቸውን ተግባራት ይወስናል ፣ በተዛማጅ ለሚሠሩ ተግባራት በዚህ መመሪያ እና በህግ የሚፈቀደውን አስፈላጊውን ማበረታቻ ያደርጋል፡፡
11. በየወሩ የቆጣሪ አንባቢ ማህበራት ያነበቡትን ንባብ ፈርሞ ይረከባል ፣ ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል ፣ ድጋሚ ሊነበቡ የሚገባቸውን ቆጣሪዎች ይወስናል ፡፡
12. ከቆጣሪ ንባብ ጋር ተደምረው የሚሠሩ ተግባራትን የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል ፣ ግብረ መልስ ይሰጣል ፣ ማበረታቻ የሚገባቸውን መልካም አፈጻጸሞች ይለያል ፣ ያበረታታል፡፡
13. የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም የቆጣሪ ንባብ ተግባር አፈጻጸምን ይቆጣጠራል ፣ ከቆጣሪ ንባብ አንጻር የአገልግሎት አሰጣጡ ያለበትን ደረጃ ይገመግማል ፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
14. የቆጣሪ አንባቢዎች የሥራ አፈጻጸም እና ስነምግባርን በተመለከተ በደንበኞች ያስገመግማል ፣ ከደንበኞች በተገኙ መረጃዎች ላይ መሠረት በማድረግ የቆጣሪ አንባቢ ማህበራት አባላትንም ሆነ ማህበሩን ይቀጣል ፣ ያግዳል ወይም ውላቸውን ይሰርዛል፡፡
15. የቆጣሪ ንባብ ማህበራት በዚህ መመሪያ እና አግባብ ባለው ህግ መሠረት የተጣለባቸውን ግዴታዎች በአግባቡ ፈጽመው ሲገኙ በየወሩ ክፍያ ይፈጽማል፡፡
16. የቆጣሪ አንባቢ ማህበራት ውል እንዲሰረዝ ወይም እንደገና እንዲታደስ የቀረበ ማመልከቻን በመቀበል እንዲሰረዝ ወይም እንዲታደስ ያደርጋል፡፡

17. የቆጣሪ ንባብ ሥራን ሊያቀላጥፉ እና የደንበኞችን እርካታ ሊያረጋግጡ የሚችሉ አሠራሮችን እና ቴክኖሎጂዎችን በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

## <u>አንቀፅ 5</u>

## <u>የቆጣሪ ንባብ ፣ ቢል ዝግጅትና ሽያጭ ኬዝ ቲም ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የቆጣሪ ንባብ ፣ የቢል ዝግጅት እና ሽያጭ ተግባራትን በበላይነት ይመራል ፣ ያስተባብራል፡፡
2. የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪዎችን ይመድባል ፣ ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ የማይወጡ የአንባቢ አስተባባሪዎች ላይ እርምጃ ይወሳዳል ፡፡
3. የቆጣሪ ማንበቢያ መጽሃፍ ያዘጋጃል ፣ ለአንባቢ አስተባባሪዎች ያስረክባል ፣ ሁሉም መጽሃፍ ለአንባቢ መሰጠቱን ያረጋግጣል ፡፡
4. የሁሉም ደንበኞች የውሃ ቆጣሪ በየወሩ መነበቡን ያረጋግጣል ፣ ያልተደረሰበት ደንበኛ ቤት መኖሩን ሲያውቅ ወይም ሲለይ እርምጃ ወስዶ እንዲነበብ ያደርጋል ፡፡
5. አንድ ቆጣሪ አንባቢ በወር ውስጥ እንዲያነብ የተሰጠው ደንበኞችን ቆጣሪ ንባብ እና የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ በሳምፐል ቀለበት በማሠር ካነበበው ንባብ ጋር ያመሳክራል ፣ ከሚጠበቀው በላይ ወይም በታች ልዩነት ካለው የቆጣሪ አንባቢው ማህበር ላይ እርምጃ ይወስዳል ፡፡
6. የቆጣሪ ንባብን አኖማሊስ በወቅቱ ሳይዘገይ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደጋፊ የስራ ሂደት መላኩን ያረጋግጣል፡፡
7. የተሳሳቱ ወይመ ስህተት የተገኘባቸውን የቆጣሪ ንባቦችን እንዲጣሩ ወይም በድጋሚ እንዲነበቡ ያደርጋል፡፡
8. የደንበኞችን ቅሬታ ይቀበላል ፣ ያጣራል ፣ ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል ፡፡
9. ጥራት ያለው የቆጣሪ ንባብ ሥራ በማሰራት ትክክለኛ ቢል እንዲታተም ያደርጋል፡፡
10. ከማንበቢያ መጽሃፍ ላይ የተነበበውን የቆጣሪ ንባብ ወደ ኮምፒተር በትክክል መግባቱን ያረጋግጣል ፣ ወቅታዊ ንባብ እና የውሃ ሂሳብን ከቀድሞው የደንበኛው አጠቃቀም ጋር ያገናዝባል ፡፡
11. ደንበኞች የውሃ ሂሳባቸውን በወቅቱ እንዲከፍሉና የገቢ አሰባሰቡ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል ፡፡
12. የየወሩ የውሃ ሂሳብ ለክፍያ ተቋም በወቅቱ መተላለፋቸውን ያረጋግጣል ፣ የክፍያ ተቋሙም አገልግሎቱን ለደንበኞች በተገቢው ሁኔታ እየሰጠ መሆኑን ይከታተላል፡፡

13. የክፍያ ተቋሙ ከደንበኞች የሰበሰበውን ገንዘብ በየወሩ ወደ ባለስልጣኑ የተፈቀደ የባንክ የሂሳብ ቁጥር ገቢ እያደረገ መሆኑን ይከታተላል ፣ ያረጋግጣል፡፡

14. ትክክለኛ ያልሆኑ የደንበኛ የውሃ ሂሳቦች ካሉ በበቂ መረጃ እና ማስረጃ በማስተደገፍ እንዲታረሙ ያደርጋል ፡፡

15. የታረሙ ቢሎችን ለቅርንጫፉ ፋይናንስ እና ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደጋፊ የስራ ሂደት ያሳውቃል ፡፡

16. ውዝፍ የውሃ ሂሳብ ያለባቸውን ደንበኞች ይለያል ፣ ሁለት ወር እና ከዚያ በላይ ውዝፍ ያለባቸውን ደንበኞች በሳምንት ሁለት ጊዜ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በመላክ እንዲከፍሉ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡

17. የህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት የሁለት ወርና ከዚያ በላይ የውሃ ውዝፍ ሂሳብ ሲኖርባቸው በሳምንት 3 ጊዜ ተከታታይ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በመላክ እንዲከፍሉ ማስጠንቀቂ ይሰጣል ፣ማስጠንቀቂውንም እየፈረሙ እንዲረከቡ ያደርጋል፡፡

18. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 17 እና 18 መሠረት ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ቢላክላቸውም ውዝፍ የውሃ ሂሳባቸውን ያልከፈሉ ደንበኞች አገልግሎት እንዲቋረጥ ለውሃ ደንበኞች አገልግሎት ክለርክ ሪፖረት ያደርጋል ፣ ቆጣሪው መነሳቱንም ያረጋግጣል ፡፡

19. በውዝፍ ሂሳብ ምክንያት የውሃ አገልግሎት የተቋረጠባቸው ደንበኞች ያለባቸውን ውዝፍ ሂሳብ እና የቆጣሪ ማስቀጠያ ሂሳብ መክፈላቸው ሲረጋገጥ ፣ የተቋረጠው አገልግሎት መልሶ እንዲቀጠል የሥራ ትእዛዝ ይሰጣል ፣ ሥራው በተቀመጠለት ስታንዳርድ መሠረት መፈጸሙን ያረጋግጣል ፡፡

20. ውዝፍ ሂሳብ ያለበት ደንበኛ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውዝፍ ሂሳቡን ቀርቦ ካልከፈለ እና በተቀማጭ ካስያዘው ገንዘብ በታች ከሆነ ሂሳቡን አወራርዶ ቀሪውን ገንዘብ ደንበኛው ቀርቦ እንዲረከብ በማድረግ ውሉን በመሰረዝ የውሃ መስመር ቅጥያውን ከመነሻው እንዲቋረጥ የስራ ትእዛዝ ይሰጣል ፣ስራውም በተቀመጠለት ስታንዳርድ መሰረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፡፡

21. የውሃ ቆጣሪ በእዳ ተነስቶባቸው እዳቸውን በሁለት ወር ( 60 ቀናት ) ውስጥ ከፍለው አገልግሎቱ እንዲቀጥል ያላደረጉ ደንበኞች ቢል እንዳይታተምላቸው የዲስ ኮኔክሽን የሥራ ትእዛዝ ሞልቶ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደጋፊ የስራ ሂደት ይልካል ፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል ፡፡

22. ውዝፍ ሂሳብ ያለበት ደንበኛ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውዝፍ ሂሳቡን ቀርቦ ካልከፈለ እና በተቀማጭ ካስያዘው ገንዘብ በላይ ከሆነ ደንበኛውን ተከታትሎ እንዲከፍል ማሳወቅ ፣ ደንበኛው

ሂሳቡን ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነም ባለው አሠራር መሠረት ክስ እንዲመሠረት ለህግና ኢንሹራንስ ደጋፊ የስራ ሂደት አስፈላጊውን መረጃ ይልካል፣ የህግ ሂደቱንም ይከታተላል፡፡

23. የውሃ ቆጣሪ ደንበኛው ቤት ሳይገኝ ቢቀርና የውሃ ቆጣሪው እንዲነሳ የተሰጠ የሥራ ትእዛዝም ከሌለው በደንበኛው ቤት በመገኘት ቆጣሪው በቦታው ላይ ያልተገኘበትን ምክንያት በማጣራት የውሃ መስመሩን ከመነሻው እንዲቋረጥ በማድረግ የመጨረሻውን ሲስተም ላይ ያለውን ንባብ ሞልቶ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደጋፊ የስራ ሂደት በመላክ የቢል ህትመት እንዲቋረጥ ያደርጋል፡፡

24. ቆጣሪው የጠፋበት ደንበኛ በባለስልጣኑ አሠራርና ህግ መሠረት ማሟላትና መክፈል ያለበትን ከከፈለ በኃላ የውሃ መስመሩ መልሶ እንዲቀጠልለት ሲጠይቅ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ያደርጋል፡ ፡

25. ዜሮ ንባብ ለተከታታይ ሶስት ወር በአንድ ቆጣሪ ንባብ ላይ ሲመጣ በቆጣሪ አንባቢው በኩል ለደንበኛው የማስጠንቀቂያ ይልካል ፣ የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪዎችም በአካል በደንበኛው ቤት በመገኘት ምክንያቱን እንዲያጣሩ ደርጋል፡፡

26. ዜሮ ንባብ ለስድስት ወራት በተከታታይ ተነቦ የሚመጣበትን የውሃ ቆጣሪ ካለማስጠንቀቂያ እንዲነሳ እና መስመሩም ከመነሻው እንዲቋረጥ ያደርጋል ፡፡

27. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 26 መሠረት የውሃ ቆጣሪ ተነስቶባቸው በሁለት ወር ( 60 ቀናት ) ውስጥ ቀርበው አገልግሎቱን እንዲቀጥል ያላደረጉ ደንበኞች ቢል እንዳይታተምላቸው የዲስ ኮኔክሽን የሥራ ትእዛዝ ሞልቶ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂደጋፊ የስራ ሂደት ይልካል ፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል ፡፡

28. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 21፣23 እና 27 መሠረት ቢል እንዳይታተምላቸው የተደረጉ ደንበኞች እስከ 6 ወራት ጊዜ ውስጥ ቀርበው አስፈላጊውን ሁሉ በመፈጸም የውሃ ቆጣሪው እንዲቀጠል ካላደረጉ ከባለስልጣኑ ጋር ያላቸው የደንበኝነት ውል ለሁሌም እንዲቋረጥ (Deletion) ቅጽ በመሙላት ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደጋፊ የስራ ሂደት ይልካል ፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል ፡፡

29. ተመላሽ ቢል የመሸጥ ስራ ይሰራል ፡፡

30. የቆጣሪ አንባቢ ማህበራትን የጊዜ ሠሌዳ በማዘጋጀት ያወያያል ፣ ይገመግማል ፣ መልካም አፈጻጸም ያላቸውን እና ደካማ አፈጻጸም ያላቸውን በመለየት ለውሃ ደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## አንቀፅ 6

## የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ ተግባርና ኃላፊነት

1. የቆጣሪ ንባብ ተግባርን ያስተባብራል ፣ ይመራል፣ይቆጣጠራል ፡፡
2. የማንበቢያ መጽሃፍ ከቆጣሪ ንባብ ፣ ቢል ዝግጅትና ሽያጭ ኬዝ ቲም በመረከብ ለአንባቢ ማህበራት ያስረክባል ፡፡
3. የደንበኞች ቆጣሪ ማንበቢያ ካርዶችን ለቆጣሪ አንባቢዎች አስፈርሞ ያስረክባል ፣ ካርዶቹም ለደንበኞች መታደላቸውን ያረጋግጣል ፡፡
4. በዚህ መመሪያ ወይም በባለስልጣኑ አሠራር መሠረት በየወሩ የተመደበለትን ሳምፕል ንባብ ይፈጽማል ፣ በደንበኞች የንባብ ካርድ ላይ የደንበኞች የውሃ አጠቃቀም በየወሩብ ትክክል መመዝገቡን ያረጋግጣል ፣ በቆጣሪዎች ላይ ቀለበት በማሰር ወይም የተለያዩ አሠራሮችን በመጠቀም የንባብ ጥራትን ያረጋግጣል፡፡
5. በስታንደርዱ መሰረት በየወሩ ለናሙና ንባብ ከተመረጡ 5 በመቶ መደበኛ የውሃ አገልግሎት ደንበኞችን ቆጣሪ በማንበብ የማንበቢያ ቅጹን በሁለት ኮፒ በማዘጋጀት አንዱን ኮፒ በፖስታ አሽጎ ወር በገባ 10ኛ ቀን ለቆጣሪ ንባብ ፣ቢል ዝግጅትና ሽያጭ አስተባባሪ ያስረክባል ፡፡
6. በስታንደርዱ መሰረት በየወሩ ለናሙና ንባብ ከተመረጡ 20 በመቶ ከፍተኛ እና መካከለኛ የውሃ አገልግሎት ደንበኞችን ቆጣሪ በማንበብ የማንበቢያ ቅጹን በሁለት ኮፒ በማዘጋጀት አንዱን ኮፒ በፖስታ አሽጎ ወር በገባ 10ኛ ቀን ለቆጣሪ ንባብ ፣ ቢል ዝግጅትና ሽያጭ አስተባባሪ ያስረክባል ፡፡
7. የወር የውሃ አጠቃቀማቸው 501 ሜትር ኪዩብ እና በላይ የሆኑ ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ ደንበኞች የየወሩን የቆጣሪ ንባብ እና የውሃ አጠቃቀም ሁኔታ ከቀደሙት ሶስት ወራት ጋር በማነጻጸር የውሃ አጠቃቀማቸውን እና የውሃ ቆጣሪውን ደህንነት ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣ የክትትል ስልት ይነድፋል፡፡
8. የወር የውሃ አጠቃቀማቸው ከ20 ሜትር ኪዩብ እስከ 500 ሜትር ኪዩብ የሆኑ መካከለኛ የውሃ ተጠቃሚ ደንበኞች የየወሩን የቆጣሪ ንባብ እና የውሃ አጠቃቀም ሁኔታ ከቀደሙት ሶስት ወራት ጋር በማነጻጸር የውሃ አጠቃቀማቸውን እና የውሃ ቆጣሪውን ደህንነት ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል ፣ የክትትል ስልት ይነድፋል ፡፡
9. የአዲስ ቅጥያ ቆጣሪ ንባብ ተነቦ እስኪመጣ ድረስ ለሁለት ወር ብቻ የዝቅተኛ የውሃ አጠቃቀም ከፍተኛ መጠን የሆነውን በወር 20 ሜትር ኪዩብ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት የማስተላለፍ ሥራ ይሠራል ፣ የአዲሱ ቆጣሪ ትክክለኛ ንባብ ተነቦ ሲመጣ ከተከፈለበት የውሃ መጠን ጋር የማወራረስ ወይም የማስተካከል ሥራ እንዲሠራ ያደርጋል ፡፡

10. የቆጣሪ ንባብ ወቅት ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ ንባቡ ለለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ለምዝገባ (encoding) እስኪላክ ድረስ በስሩ ያሉትን ወይም የሚስተባብራቸውን የማንበቢያ መጽሃፎችን ንባብ በናሙና ንባብ ከተወሰዱት ንባቦች ጋር በማነጻጸር ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል፡፡

11. ለንባብ ሥራ ክትትል የተቀመጡ ቀለበቶች በሙሉ መመለሳቸውን ያረጋግጣል ፣ ካልተመለሱ ቀለበት የታሰረባቸውን ደንበኞች ንባብ ሳይነበብ በግምት የተሞላ እንደሆነ አድርጎ በመውሰድ በአንባቢ አስተባባሪ የተነበበውን ንባብ በትክክለኛ ንባብ በመጠቀም አንባቢው ክፍያ እንዳይፈጸምለት ያደርጋል፡፡

12. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት ሳይመለስ የቀረውን ቀለበት ከአንባቢው ጋር በጋራ በመሆን ደንበኛው ቤት ድረስ በመሄድ በመመዝገብ ቀለበቱ እንዲመለስ ያደርጋል ፣ አንድ አንባቢ በአንድ ወር ያልመለሰው የቆጣሪ ቀለበት ቁጥር ብዛት እስከ 10 ቀለበት ከሆነ አንባቢው ማህበሩ የአገልግሎት ክፍያው የማይፈጸምለት ሆኖ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ያደርጋል ፡፡

13. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት ሳይመለስ የቀረውን ቀለበት ከአንባቢው ጋር በጋራ በመሆን ደንበኛው ቤት ድረስ በመሄድ በመመዝገብ ቀለበቱ እንዲመለስ ያደርጋል ፣ አንድ አንባቢ በአንድ ወር ያልመለሰው የቆጣሪ ቀለበት ቁጥር ብዛት 10 እና ከዚያ በላይ ቀለበት ከሆነ አንባቢው የወሩ ትክክለኛ የንባብ ክፍያ 25 በመቶ እንዳይከፈለው በማድረግ እንዲቀጣ ያደርጋል ፡፡

14. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት ሳይመለስ የቀረውን ቀለበት ከአንባቢው ጋር በጋራ በመሆን ደንበኛው ቤት ድረስ በመሄድ በመመዝገብ ቀለበቱ እንዲመለስ ያደርጋል ፣ አንድ አንባቢ በአንድ ወር ያልመለሰው የቆጣሪ ቀለበት ቁጥር ብዛት ከታሰረው ቀለበት 25 በመቶ እና ከዚያ በላይ ከሆነ አንባቢው ስራውን ማህበሩ ለሚተካው አንባቢ አስረክቦ እንዲሰናበት ያደርጋል ፡፡

15. ቆጣሪ አንባቢዎች በምክንያታዊ ኮድ ( Reason Code ) የሚመልሷቸውን ቆጣሪዎች ትክክለኛነት የተለያዩ መንገዶች በመጠቀም ያጣራል ፣ ይከታተላል ፣ የሃሰት ምክንያታዊ ኮድ ሞልተው የሚመጡ አንባቢዎችን በመከታተል እርምጃ በማህበሩ በኩል እንዲወሰድ ያደርጋል ፡፡

16. ቆጣሪ አንባቢዎች የሚያቀርቧቸውን የቆሙ ቆጣሪዎች ፣ የቆሸሹ ቆጣሪዎች ፣ የቴክኒክ ችግር ያለባቸውን ውሃ መስመሮች ወይም ቆጣሪዎች እንዲስተካከሉ ወይም እንዲታዩ አስፈላጊውን የሥራ ትእዛዝ በመሙላት ለውሃ ደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት ክለርክ ያስተላልፋል፣ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን ይከታተላል ፡፡

17. የቆጣሪ አንባቢዎች አንብበው ያመጡትን መጽሃፍ ንባብ ትክክለኛነት አረጋግጦ ይረከባል ፣ የተነበበውን ንባብ ለቆጣሪ ንባብ ፣ ቢል ዝግጅትና ሽያጭ ኬዝ ቲም አስፈርሞ ያስረክባል፡፡

18. የቆጣሪ ንባብ ወደ ኮምፒተር ሲመዘገብ ችግር የታየባቸውን እና ተመሳሽ የሆኑ ንባቦች እንዲጣሩ ወይም በድጋሚ እንዲነበቡ ለአንባቢ ማህበራት ያስረክባል ፣ በተቀመጠለት ጊዜ ውስጥ ንባቡ ተስተካክሎ መነበቡን ያረጋግጣል ፡፡

19. የቆጣሪ አንባቢዎች በምክንያታዊ ኮድ ( Reason Code ) ሪፖርት ያደረጓቸው ደንበኞች ቆጣሪዎች ከሁለት ወር በላይ ሳይስተካከሉ የቆጣሪ ግብር ብቻ ይዘው የሚወጡ ከሆነ በአካል ደንበኞቹ ቤት በመገኘት ያጣራል ፣ አግባብነት ያለውን እርምጃ ይወስዳል ፡፡

20. ዜሮ ንባብ ለተከታታይ ሶስት ወራት ጊዜ በአንድ ቆጣሪ ንባብ ላይ ሲመጣ በአካል ደንበኛው ቤት በመገኘት ምክንያቱን ያጣራል ፣ አግባብነት ያለውን እርምጃ ይወስዳል ፡፡

21. ደንበኞች በተለያየ ምክንያት ቀድመው ከፍተኛ የውሃ ፍጆታ ዋጋ ከከፈሉ (OVC) እነዚህን ደንበኞች ለይቶ በየወሩ የመከታተያ ቅጽ ላይ በመመዝገብ ወደ ትክክለኛው የቢል ስርአት እንዲገቡ ያደርጋል ፡፡

22. ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደጋፊ የስራ ሂደት የሚላከውን አኖማሊስ ለቆጣሪ አንባቢዎች በመመዝገብ ያከፋፍላል ፣ በተገቢው ጊዜ ውስጥ አንባቢው አስተካክሎ እንዲመልስ ያደርጋል፡፡

23. በቆጣሪ አንባቢዎች ተስተካክሎ የቀረበለትን አኖማሊስ አጣርቶ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደጋፊ የስራ ሂደት ያስረክባል፣

24. ከደንበኞች የሚቀርቡ የንባብ ስህተት ቅሬታዎችን ይቀበላል ፣ በአካል ደንበኛው ቤት በመገኘት ቅሬታውን ያጣራል ፣ ደንበኞችን ቆጣሪ አንባቢው ባለበት ያወያያል ፣ የችግሩን መነሻ በማጣራት እርምጃ ይወስዳል፡፡

25. የቆጣሪ አንባቢዎችን የሥራ አፈጻጸም መከታተያ መዝገብ በማዘጋጀት በየወሩ የአንባቢውን አፈጻጸም ፣ የቆጣሪ ንባብ ስህተት ፣ የደንበኞች ቅሬታ እና በተጓዳኝ የተሰጡ ተግባራትን አፈጻጸም ይመዘግባል ፡፡

## <u>አንቀፅ 7</u>

## <u>የቆጣሪ አንባቢ ኢንተርፕራይዞች ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የቆጣሪ አንባቢ ማህበራት ለቆጣሪ ማንበብ ሥራ የሚፈለገውን የትምህርት መስፈርት የሚያሟሉ አባላት ሊኖሩት ይገባል፡፡
2. የማህበሩ አባላት እና አመራሩ በሙሉ በቆጣሪ ንባብ ሥራ ላይ እንዲሠማሩ ማድረግ አለበት፡፡
3. የማህበሩ አመራርና አባላት ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ባለስልጣኑ የሚያዘጋጀውን ስልጠና እንዲወስዱ ማድረግ አለበት፡፡፡

4. የማህበሩ አባላት መልካም ስነምግባር ያላቸው ፣ በማንኛወም ሱስ ያልተያዙ ፣ ከሚኖሩበት ወረዳ የመልካም ስለምግባር ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚችሉ ፣ በወንጀል ያልተቀጡ እና በእግር ተንቀሳቅሶ ለመሥራት የሚያስችል የጤና ሁኔታ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

5. የማህበሩ አመራሮችና አባላት ለውሃ ደንበኞች ደህንነት ሲባል በባለስልጣኑ የሚጠየቁትን ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፡፡

6. ወርሃዊ የቆጣሪ ንባብ ፕሮግራሙን ደንበኞች እንዲያውቁት ለማድረግ ሲባል የባለስልጣኑ ማህተም ያረፈበት ጥራቱን የጠበቀ ማስታወቂያ የንባብ ሠራተኛውን ስም ፣ መቼ የት ሰፈር የንባብ ሥራውን እንደሚሠራ በወረዳ አስተዳደር ጽ/ ቤት ሠሌዳ እና ዘወትር ህዝብ በሚያይበት ቦታዎች መለጠፍ አለበት፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተጠቀሰው የህዝብ ማስታወቂያ እንዳይበላሽ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ሲበላሽ ወይም የአንባቢ ለውጥ ሲኖር የተስተካከለ ማስታወቂያ አንባቢው ወደ ሥራ ከመሠማራቱ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ መለጠፍ አለበት፡፡

8. የቆጣሪ አንባቢ ወደ ሥራ ሲሠማራ ለደንበኞች ገላጭ የሆነ ባለስልጣኑ የመረጠውን የቀለም አይነት ዩኒፎርም ወይም ጋዎን በማዘጋጀት ማልበስ አለበት ፣ በዩኒፎርሙ ጀርባ እና በቀኝ ደረት ላይ የባለስልጣኑ አርማ እና በግራ ደረት ላይ የማህበሩ አርማ በግልፅ የሚታይ ሁኔታ ሊታተምበት ይገባዋል፡፡

9. የቆጣሪ አንባቢዎች ቅርንጫፉ በሚሰጠው በቆጣሪ አንባቢ ደንበኛ ጥመርታ ስሌት መሠረት ብቻ አንባቢዎቹ የሚያነቡትን የቆጣሪ ብዛት ይመድባል፡፡

10. የአዲስ ደንበኛ ቆጣሪ ንባብ ለማህበሩ ሲጨመርለት አካባቢውን መሠረት በማድረግ ለቆጣሪ አንባቢዎች ይደለድላል፡፡

11. የቆጣሪ አንባቢዎች በሥራ ላይ ሲሰማሩ በሚያነቡት መጽሃፍ ውስጥ ያልተካተተ በሚያነቡበት ሠፈር የማይነበብ ቆጣሪ ካጋጠማቸው የውሃ ቆጣሪው ባለቤት ስም ፣ አድራሻ እና የቆጣሪ ቁጥር በመመዝገብ ከ 10 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት ፡፡

12. ከቆጣሪ ንባብ ውጪ የማህበሩ አባላት በማንኛውም አይነት የውሃ ቴክኒክ ሥራዎች ማለትም የውሃ መስመር ጥገና ፣ የቆጣሪ መቀጠል ፣ ቆጣሪ ማንሳት ፣ ቆጣሪ ማጽዳት ፣ ቆጣሪ ምርመራ እና ጥገና እና በመሳሰሉት ስራዎች ላይ በሥራ ሰዓትም ሆነ ከሥራ ሰዓት ውጪ ሊሠማሩ አይችሉም ፣ ማህበሩም አንባቢዎች በማንኛውም የውሃ ቴክኒክ ሥራ ላይ ያልተሰማሩ እና በዚህ ስራ ላይ እስካሉበት ግዜ ድረስም የማይሰማሩ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

13. የቆጣሪ አንባቢዎች ደንበኞች ከባለስልጣኑ ጋር ባላቸው የውል ግዴታ መሀል ጣልቃ መግባት ፣ ጉዳይ ማስፈጸም ፣ የውሃ ቢል መክፈል እና በመሳሰሉት ጉዳዮች እንዳይሳተፉ እና በዚህ መመሪያ ከተሰጡጣቸው ተግባርና ኃላፊነት ውጪ እንዳይንቀሳቀሱ ማድረግ እና መቆጣጠር አለበት፡፡

14. የቆጣሪ አንባቢዎች ከደንበኞች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ፣ ለደንበኞች ተገቢው ክብር እንዲሰጡ ፣ ለንባብ ሥራ ሲሠማሩ ማንኛውንም 3ኛ ወገን ወይም ግለሰብ ይዘው መንቀሳቀስ እንደማይችሉ ፣ አልኮል ጠጥቶ ወይም ጫት ቅሞ ወደ ደንበኛ ቤት መግባት ወይም መንቀሳቀስ እንደማይችሉ ፣ ምንም አይነት የጦር መሳሪያ ይዘው መሰማራት እንደማይችሉ የሚገልፅ እና የሚስገድድ የስነምግባር ግዴታ ማስፈረም አለበት ፣ ለአፈፃፀሙም ጥብቅ ክትትል ማድረግ እና ኃላፊነት መውሰድ ይወስዳል፡፡

15. ደንበኞች በቆጣሪ ንባብ ሥራ ላይ ወይም በውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ላይ የሚያቀርቡትን ቅሬታ ተቀብሎ ለባለስልጣኑ ማስተላለፍ አለበት፡፡

16. አንባቢዎች ለንባብ ሲንቀሳቀሱ ደንበኞች በቤታቸው ካልተገኙ አንባቢው በቀጣይ ቀን በድጋሚ በመምጣት የሚያነብበትን ቀንና ሰዓት ማስታወቂያ ወይም ማስታወሻ በደንበኛው ቤት ዋና በር ላይ እንዲለጥፍ ማድረግ አለበት፡፡

17. የባለስልጣኑ ለደንበኞች የሚያስተላልፈውን ማስታወቂያ ፣ማስጠንቀቂያ፣ መጥሪያ ፣ ብሮሸርሽ ፣ እና የመሳሰሉትን ለደንበኞች ያደርሳል፡፡

18. የባለስልጣኑ በህግ በተሰጠው ስልጣን ፣ የህግ ግዴታ እና ሃላፊነት ወሰን ውስጥ ሆኖ የመስራት ሃላፊነት አለበት፡፡

## <u>አንቀፅ 8</u>

## <u>የውሃ ቆጣሪ አንባቢ ተግባርና ሃላፊነት</u>

1. የየወሩን የውሃ ቆጣሪ ማንበቢያ የጊዜ ሰሌዳ ( ፕሮግራም ) ለደንበኞች በማሳወቅ እና በወረዳ ጽ/ ቤቶች ፣ በጋራ መኖሪያ ቤቶች ፣ በየዞኑ በግልፅ ሊታይ በሚችል ቦታ ማስታወቂያ በመለጠፍ በፕሮግራሙ መሠረት በየቤቱ በመሄድ ንባብ ያካሂዳል፡፡

2. አንባቢው ደንበኞች የንባብ ካርድ እንዲኖራቸው ማድረግ አለበት ፣ የንባብ ካርድ የሌላቸው ደንበኞች ካጋጠሙ ዝርዝሩን በመያዝ በቀጣይ ወር የንባብ ካርድ ይሰጣል፡፡

3. በቀዳሚ ወር 28ኛ ቀን የማንበቢያ መጽሃፍ በመረከብ ቤት ለቤት በመሄድ የውሃ ቆጣሪ ንባብ በመፈጸም ቀጣይ ወር በገባ በ 20ኛው ቀን ያነበበበትን መጽሃፍ ለቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ ያስረክባል ፡፡

4. የደንበኞች ወርሃዊ ፍጆታ የተዛባ እንዳይሆን ለማድረግ ይቻል ዘንድ የንባብ ግዜው በየወሩ በተመሳሳይ ቀን ወይም አንድ ቀን ወደ ኃላና ወደ ፊት ብቻ እንዲሆን በማድረግ በአካል በመገኘት ብቻ ንባብ ይወስዳል ፡፡

5. በየወሩ ንባብ ከደንበኞች ቆጣሪ በሚወሰድበት ወቅት በደንበኛው ቤት በሚገኝ የንባብ ካርድ ላይ የእለቱን ንባብ ፣ ንባብ የተወሰደበትን ቀንና ሰዓት ፣ የውሃ ፍጆታ ሂሳብ መጠን መዝግቦ በፊርማው ያረጋግጣል፡፡

6. ባለስልጣኑ በሚዘጋጀው የማንበቢያ ቅፅ/ መጽሃፍ ወይም ባለስልጣኑ የሚያቀርበውን አማራጭ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የውሃ ደንበኞች ቆጣሪ በሚገኝበት ቦታ በመገኘት የየወሩን የውሃ ቆጣሪ ንባብ ይመዘግባል፡፡

7. የውሃ ቆጣሪ በትክክል መገጠሙን ( ወይም ሮቢሾ አለመሆኑን ) ፣ የቆጣሪ ማሸጊያ ሊድ አለመበጠሱን እና የቆጣሪው ደህንነት የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል ፡፡

8. ከቆጣሪ በፊት ህገ ወጥ ቅጥያ አለመፈጸሙን ያረጋግጣል ፣ ይህ ተፈፅሞ ሲገኝ ወዲያውኑ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳውቃል ፣ ህገ ወጥ ቅጥያ ወይም ህገ ወጥ የመስመር ዝርጋታ ምልክት ወይም ጥርጣሬ ካለ ለቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ በአፋጣኝ ሪፖርት ያደርጋል ፣ በጥቆማው መሠረት እርምጃ መወሰዱን ያረጋግጣል፡፡

9. ደንበኛው ከቆጣሪ በኃላ ለሌላ ላልተፈቀደለት ግለሰብ ወይም ድርጅት የውሃ መስመሩን አሳልፎ አለመሰጠቱን ይቆጣጠራል ይከታተላል፡፡

10. የውሃ ቆጣሪ ባለስልጣኑ ባለው አሠራርና ደንብ መሠረት ከተገጠመበት ቦታ ላይ ያልተዛወረ መሆኑን ይከታተላል ያረጋግጣል፡፡

11. የውሃ ቆጣሪ ላይ ወይም አካባቢ የውሃ ቆጣሪ ንባብን የሚያውክ ግንባታ ፣ የውሻ ቤት ፣ መጸዳጃ ቤት ፣ አጥር እና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮች አለመገንባታቸውን ይከታተላል ፣ ተፈጽሞ ሲገኝም ሪፖርት ያደርጋል ፡፡

12. ከተለመደው የተለየ የተጋነነ የውሃ አጠቃቀም በመብለጥም ሆነ በማነስ ሲያጋጥም ወዲያውኑ ለቆጣሪ ንባብ አስተባባሪ ያሳውቃል፡፡

13. በንግድ ቤት ( Non Domestic ) ቆይተው ወደ መኖሪያ ቤት ( Domestic ) የተለወጡ ወይም መኖሪያ ቤት ( Domestic ) ቆይተው ወደ ንግድ ቤት ( Non Domestic ) የተለወጡ ደንበኞችን ዝርዝር እየተከታተለ በየወሩ ለቆጣሪ ንባብ አስተባባሪ ያሳውቃል፡፡

14. ባለስልጣኑ ለደንበኞቹ የሚያስተላልፋቸውን የተለያዩ ማስታወቂያዎች ፣ መረጃዎች ፣ ማስጠንቀቂያዎች ፣ እና የመሳሰሉትን ያደርሳል፡፡

15. ለሥራ ሲሠማራ ባለስልጣኑ በመረጠው ቀለም እና በጀርባ እና በቀኝ ደረት ላይ የባለስልጣኑ አርማ እና በግራ ደረት ላይ የማህበሩ አርማ በግልፅ በሚታይ ሁኔታ የታተመበትን ዩኒፎርም ወይም ጋዎን መልበስ ይኖርበታል፡፡

16. ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደጋፊ የስራ ሂደት የሚላከውን አኖማሊስ ከቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪዎች በመረከብ በሁለት ቀን ውስጥ የንባቡን ትክክለኛነት አረጋግጦ ይመልሳል፡፡

17. ፣ከማህበሩ ሃላፊዎች ጋር በወር አንድ ጊዜ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በመገኘት ወርሃዊ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፡፡

18. ባለስልጣኑ በሚያዘጋጀው ሳምንታዊም ሆነ ሌሎች የመሰብሰቢያ ፕሮግራሞች ላይ ሰዓት አክብሮ ይገኛል ፣ በባለስልጣኑ በሚዘጋጀው የአቅም ግንባታ ስልጠና ላይ በንቃት ይሳተፋል፡፡

## አንቀፅ 9

## የውሃ ቆጣሪ አንባቢዎች ተጓዳኝ / ተጨማሪ ተግባርና ሃላፊነት

1. የቆጣሪ አንባቢው በተመደበበት ክልል ለሥራ ሲዘዋወር የውሃ ስርጭት በታቀደው መሠረት ያልተፈጸመ ከሆነ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2. ቆጣሪ አንባቢው ንባብ ባካሄደባቸው ቤቶች ውሃ በፈረቃቸው እየታደለ መሆኑን አለመሆኑን ጠይቆ በማረጋገጥ መረጃውን በመያዝ በፈረቃቸው ውሃ የማያገኙ ቤቶች ሲያጋጥሙ ወዲያውኑ ለቅርንጫፍ ጽ/ ቤቱ ያሳውቃል፡፡

3. የሚያፈስ የውሃ መስመር ሲያጋጥመው ወዲያውኑ መረጃውን በመመዝገብ ለሚመለከተው ክፍል ያሳውቃል እንዲሁም መስሩር መጠገን እና አለመጠገኑን በመከታተል በቀጣይ ጊዜ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. በተመደበበት ክልል ህገ ወጥ ቅጥያን ይከታተላል ይቆታጠራል ፣ ተፈጽሞ ሲገኝም ወዲያውኑ መረጃውን መዝግቦ ያሳውቃል ፣ ህገ ወጥ ድርጊቱ ላይ እርምጃ መወሰድና አለመወሰዱን በመከታተል አጣርቶ በቀጣይ ለቆጣሪ ንባብ አስተባባሪ ያሳውቃል፡፡

5. በህግ ወይም በመመሪያ ከተፈቀደው ውጭ የውሃ አገልግሎቱን አላግባብ ሲጠቀም ወይም ለሌላ አገልግሎት ሲያውል የተገኘ ደንበኛን አድራሻውን በመመዝገብ ለቆጣሪ ንባብ አስተባባሪ ያሳውቃል፡ :

6. በውሃ መስመር ላይ ህገ ወጥ ግንባታ ( የመንግስት የውሃ መስመር የሚያልፍበትን ቦታ ማጠር ፣ በውሃ መስመር ላይ መንገድ መገንባት ፣ በውሃ መስመር ላይ የፍሳሽ ማስተላለፊያ ዲች መገንባት ፣ በውሃ መስመር ላይ ጋራዥ ወይም ጋራዥ ዘይት የሚያልፍበት ወይም የሚጠራቀምበት ሁኔታ መፍጠር ፣ ወ.ዘ.ተ. ) በግለሰብም ሆነ በተቋማት ሲፈጸም ለሚመለከተው የባለስልጣኑ የስራ ክፍል ያሳውቃል፡፡

7. የውሃ መበከል ወይም ድፍርስነት ያለባቸው አካባቢዎች ሲያጋጥም ወዲያውኑ መረጃውን በመመዝገብ ለሚመለከተው ክፍል ማሳወቅ እንዲሁም ጥቆማውን በመጠቀም የማስተካከያ ርምጃ መወሰዱንና አለመወሰዱን ተከታትሎ በቀጣይ ጊዜ ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

8. ለረዥም ( ከሶስት ወር በላይ ) ጊዜ ሂሳብ ሳይከፍሉ ውሃ የሚጠቀሙ ወይም ቢል የማይወጣላቸው ደንበኞች ሲያጋጥሙ ወይም መረጃ ሲሰማ መረጃውን ለቆጣሪ ንባብ አስተባባሪ ያሳውቃል፡፡

9. አዲስ የውሃ አገልግሎት ቅጥያ ኖሯቸው ነገር ግን ቢል የማይወጣላቸው ደንበኞች ሲያጋጥሙ መረጃውን በጽሁፍ መዝግቦ ለቆጣሪ ንባብ አስተባባሪ ያሳውቃል፡፡

10. የባለስልጣኑ የውሃ ደንበኛ የሆኑና ያልሆኑ የቤት ባለቤቶችን መዝግቦ መረጃ እንዲያመጣ ሲጠየቅ በሚሰጠው ቅጽ መሠረት ይመዘግባል ለዚህም ባለስልጣኑ የማበረታቻ ክፍያ ሊፈጽም ይችላል ፣

11. በተጨማሪም ሌሎች እንደ ወቅቱ ሁኔታ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በማበረታቻ ወይም በቀጥታ የሚሰጠውን ተጨማሪ የሥራ ትእዛዝ መፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## የቆጣሪ ንባብ ስርዓት እና ክፍያ አፈፃፀም

## አንቀፅ 10

### የቆጣሪ አንባቢና ደንበኞች ጥመርታ

1. በማስፋፊያና ተራራማ አካባቢዎች አንድ ቆጣሪ አንባቢ እስከ 1,200 ደንበኞች የውሃ ቆጣሪ ማንበብ አለበት ፣
2. በመሃል ከተማ አንድ ቆጣሪ አንባቢ እስከ 1,725 ደንበኞች የውሃ ቆጣሪ ማንበብ አለበት ፣
3. በኮንደሚኒየም ቤቶች አንድ ቆጣሪ አንባቢ እከከ 1,850 ደንበኞች የውሃ ቆጣሪ ማንበብ አለበት ፣

4. ባለስልጣኑ የውሃ ቆጣሪ ንባብ ጥራትን ለማስጠበቅ ሲባል የአንባቢና ደንበኛ ጥመርታን እንደ አስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ይችላል ።

## አንቀፅ 11

## የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪና ደንበኞች ጥመርታ

1. አንድ የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ 7500 ደንበኞች የውሃ ቆጣሪ ንባብ ሥራ መከታተል ፣ መቆጣጠር እና ማስተባበር አለበት ፣
2. አንድ የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ ከ 4 — 6 ቆጣሪ አንባቢዎችን መከታተል ፣ መቆጣጠር እና ማስተባበር አለበት ፣
3. አንድ የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ ከፍተኛ የውሃ ተጠቃሚ ከሆኑ ደንበኞች መጽሃፍ ውስጥ የደንበኞቹን 20 በመቶ በሳምፕል በመምረጥ በየወሩ ቀለበት ማሠር አለበት ፣
4. አንድ የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ የመደበኛ (ከፍተኛ ውሃ ተጠቃሚ ካልሆኑ) ደንበኞች መጽሃፍ ውስጥ የደንበኞቹን 5 በመቶ በሳምፕል በመምረጥ በየወሩ ቀለበት ማሰር አለበት ፣
5. የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ ሁሉም ቀለበቶች በቆጣሪ አንባቢዎች በየወሩ ከንባብ መጽሃፍ ጋር መመለሳቸውን በማረጋገጥ አለበት ፣ ያሰረው ቀለበት ካልተመለሰ ከቆጣሪ አንባቢው ጋር በደንበኛው ቤት በአካል በመሄድ እንዲመለስ ማድረግ አለበት ፣
6. ባለስልጣኑየውሃ ቆጣሪ ንባብ ጥራትን ለማስጠበቅ ሲባል የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪና ደንበኛ ጥመርታን እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ይችላል ፣
7. ባለስልጣኑ የቆጣሪ አንባቢ ቀለበት የሚያስርባቸውን ደንበኞች ብዛት እንደአስፈላጊነቱ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

## አንቀፅ 12

## የናሙና የቆጣሪ ንባብ አፈጻጸምና የሚያስከትለው ኃላፊነቶች

1. የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪዎች በየወሩ ከአንባቢው የጊዜ ሠሌዳ ቀድመው ለናሙና በተመረጡ ደንበኞች ቆጣሪ ላይ የንባብ መቆጣጠሪያ ቀለበት ማሠር አለባቸው ፣
2. የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ ቀለበት ባሰረባቸውን ቆጣሪዎች ምንም አይነት ህገ ወጥ ተግባር አለመፈጸሙን ያረጋግጣል ፣ ተፈጽሞ ከተገኘ ፣ የህገ ወጥ ድርጊቱን በመመዝገብ የፎቶና ሌሎች በህግ ተቀባይነት ያላቸውን ማስረጃዎች ያሰባስባል ፣

3. የቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ህገ ወጥ ተግባር በተፈጸመበት ቆጣሪ እንዲነሳ ያደርጋል ፣ በተነሳው ቆጣሪ ምትክ ሌላ የተመረጠ ቆጣሪ ላይ ቀለበት ማሠር አለበት፣

4. ቆጣሪ አንባቢአስተባባሪ የናሙና ንባብ ያደረገባቸውን ቆጣሪ ባለቤት ደንበኞች በቆጣሪ ንባብ ላይ ያላቸውን አስተያየት ለዚህ ሥራ በተዘጋጀ ቅጽ መሠረት ይቀበላል ፣ ደንበኞች ፍቃደኞች ከሆኑ የሰጡትን አስተያየት በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ ያደርጋል ፣

5. ቀለበት የታሰረባቸው ቆጣሪዎች ደንበኞች የቆጣሪ ቁጥር ፣ የውል ቁጥር ፣ ናሙና ንባብ እና አስተያየት በሚስጥር ተመዝግቦ የቆጣሪ ንባብ ፣ ቢል ዝግጅትና ሽያጭ ኬዝ ቲም መሪ እጅ መቀመጥ አለበት ፣

6. የቆጣሪ አንባቢ የደንበኞችን የቆጣሪ ንባብ ለቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ ሲያስረክብ ቀለበት የታሰረባቸውን ቆጣሪዎች ቁጥርና የውል ቁጥር መዝግቦ ከቀለበቱ ጋር በየወሩ ማስረከብ አለበት ፣

7. የቆጣሪ ንባብ ፣ ቢል ዝግጅትና ሽያጭ ኬዝ ቲም የተመለሱና ያልተመለሱ ቀለበቶችን በየወሩ ይለያል ፣ ቀለበቱ ላልተመለሰበት ንባብ ክፍያ እንዳይፈጸም ያደርጋል ፣ ቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ ናሙና አንብቦ ያመጣውን ንባብ ለኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ክፍል ያስተላልፋል፣

8. በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በቆጣሪ አንባቢ አስተባባሪ ተመዝግቦ የመጣው የደንበኞች አስተያየት ቆጣሪ አንባቢው በዚህ መመርያ አንቀጽ 8 እና 9 የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት አለመወጣቱን የሚያመላክት ከሆነ የቆጣሪ ንባብ ፣ ቢል ዝግጅትና ሽያጭ ኬዝ ቲም አንባቢውን ለቀጠረው ኢንተርፕራይዝ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ማድረግ አለበት ፣

9. በየወሩ አንድ ጊዜ የቆጣሪ አንባቢዎችና እና የማህበሩ አመራሮች በተገኙበት ስለ ስራ አፈጻጸም እና በቆጠራ ሂደት ስላጋጠሙ ችግሮች ግምገማ መካሄድ አለበት ፣የቆጣሪ ንባብ ፣ ቢል ዝግጅትና ሽያጭ ኬዝ ቲም በየወሩ የቀጣይ ወር የንባብ መጽሃፍ ለአንባቢ ከመተላለፉ በፊት ወይም ከቀጣይ ወር ከንባብ መጽሃፍ ጋር በግምገማው የተገኘውን የማህበሩን አጠቃላይ አፈጻጸም ጥንካሬና ድክመት እንዲሁም ከደንበኞች የተሰጡ አስተያያቶችን በጽሁፍ አዘጋጅቶ ለኢንተርፕራይዞቹ ወይም ማህበራቱ አስፈርሞ ያስረክባል ፣

## አንቀፅ 13

## የቆጣሪ አንባቢ ኢንተርፕራይዞች ወርሃዊ ክፍያ

1. በየወሩ በትክክል ተነቦ ለሚመጣ የቆጣሪ/ ደንበኛ ቁጥር በውሉ የተቀመጠውን የአንድ ንባብ የማንበቢያ ዋጋ በቀጥታ በትክክል በተነበበው ቆጣሪ ብዛት በማባዛት ለኢንተርፕራይዙ ይከፈላል፡፡

2. ለቆጣሪ አንባቢ ኢንተርፕራይዞች ወርሃዊ ክፍያ የሚፈጸመው ለኢንተርፕራይዙ እንዲያነብ የተሰጡ መጽሃፎች ንባብ በሙሉ በማንበቢያ ጊዜ ውስጥ ተጠቃለው በትክክል መነበባቸው ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የማንበቢያ መፅሃፍ ተጠቃሎ እንደገባ የሚረጋገጠው ወይም ለክፍያ ብቁ የሚሆነው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ደ/ የስራ ሂደት የቆጣሪ ንባብን ኢንኮዲንግ ሠርቶና እንዲታረሙ የተጠየቁ የንባብ ማጣሪያዎች (አኖማሊስ) ታርመው ሲቀርቡ ደ/ የስራ ሂደቱ ክፍያ የሚፈጸምባቸውን በትክክል የተነበቡ ንባቦች ቁጥር ለፋይናንስ ደ/ የሰራ ሂደት ሲያቀርብ ብቻ ነው፡ ፡

4. የየወሩ ክፍያ ሲፈጸም የአጠቃላይ ወርሃዊ ክፍያ ላይ 10 (አስር) በመቶ ለውል አፈጻጸም ( የጉድለት ወይም ተጠያቂነት ) ዋስትና ተቀናሽ ይደረጋል፡፡ በየወሩ ኢንተርፕራይዙ የሚፈለግበት ጉድለት ወይም ተጠያቂነት ከሌለበት በቀጣይ ወር ክፍያ ላይ የቀደመው ወር የዋስትና ተቀናሽ ተደምሮ ይከፈለዋል፡፡

## አንቀፅ 14

## የውል ግዴታን ባለመወጣት ስለሚደረግ የቅጣት ተቀናሽ

1. የቆጣሪ አንባቢ ኢንተርፕራይዝ ( ማህበር) በቆጣሪ አንባቢዎች በኩል አስነብቦ ያመጣው ንባብ ውስጥ ስህተት መፈጸሙ ከተረጋገጠ ለጠቅላላው ወርሃዊ የንባብ ሥራ ከሚከፈለው ገንዘብ ውስጥ ለአንድ ውል ቁጥር የሚደርሰው ድርሻ ተሰልቶና በተሳሳቱ ውሎች መጠን ተባዝቶ በሚገኘው ውጤት ላይ 20 (ሃያ) በመቶ ቅጣት ታክሎበት ለዋስትና ከተያዘው ገንዘብ ላይ ተቀናሽ ሆኖ ለባለስልጣኑ ገቢ ይደረጋል፡፡

2. ቆጣሪ አንባቢዎች የደንበኛው ቤት ሳይደርሱ የሃሰት ንባብ ኮዶችን ማለትም ውሃ አይደርሳቸውም ፣ በሩ ዝግ ነው ፣ ተናካሽ ውሻ አለ ፣ ቆጣሪው በጭጋግ ተሸፍኗል እና በመሳሰሉት ምክንያት የወሩን የቆጣሪ ንባብ በትክክል ሳያነቡ ቢቀሩ ፣ ያልተነበበውን ውል ተቆጥሮ ለኢንተርፕራይዙ ወይም ለመሃበሩ ለአንድ ውል ቁጥር በሚከፈለው ክፍያ ተባዝቶ በሚገኘው ውጤት ላይ 30

(ሰላሳ) በመቶ ቅጣት ታክሎበት ለዋስትና ከተያዘው ገንዘብ ላይ ተቀናሽ ሆኖ ለባለስልጣኑ ገቢ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ 15

### የቆጣሪ አንባቢዎች ለሚፈጽሙት ተጨማሪ ተግባራት ማበረታቻ

1. የሚያፈስ የውሃ መስመር ( በጊቢ ውስጥም ሆነ ከጊቢ ውጪ ) ቀድሞ የጠቆመ እና በጥቆማው መሠረት መጠገኑን ያረጋገጠ የጠቆመው የሚያፈስ መስመር ተመዝግቦ እና በቅርንጫፍ ጽ/ ቤቱ ሥራውን በሠሩት የሚመለከታቸው አካላት እና በበላይ ኃላፊዎች ውጤቱ ሲረጋገጥ ለእያንዳንዱ የተጠገነ የውሃ መስመር ማበረታቻ የ 2 ደንበኞች የንባብ ክፍያ ተሰልቶ ለቆጣሪ አንባቢው በማህበሩ በኩል የሚከፈል ይሆናል፡፡
2. ህገ ወጥ ቅጥያ ቀድሞ የጠቆመ እና በጥቆማው መሠረት እርምጃ መወሰዱን ያረጋገጠ የጠቆመው ህገ ወጥ ቅጥያ ተመዝግቦ እና በቅርንጫፍ ጽ/ ቤቱ ሥራውን በሠሩት የሚመለከታቸው አካላት እና በበላይ ኃላፊዎች ውጤቱ ሲረጋገጥ በእያንዳንዱ ህገ ወጥ ቅጥያ ማበረታቻ የ 10 ደንበኞች የንባብ ክፍያ ተሰልቶ ለቆጣሪ አንባቢው በማህበሩ በኩል የሚከፈል ይሆናል፡፡
3. በውሃ መስመር ላይ ህገ ወጥ ግንባታ መፈጸሙን ቀድሞ የጠቆመ እና በጥቆማው መሠረት እርምጃ መወሰዱን ያረጋገጠ የጠቆመው ህገ ወጥ ግንባታ ተመዝግቦ እና በቅርንጫፍ ጽ/ ቤቱ ሥራውን በሠሩት የሚመለከታቸው አካላት እና በበላይ ኃላፊዎች ውጤቱ ሲረጋገጥ በእያንዳንዱ ህገ ወጥ ግንባታ ማበረታቻ የ 5 ደንበኞች የንባብ ክፍያ ተሰልቶ ለቆጣሪ አንባቢው በማህበሩ በኩል የሚከፈል ይሆናል፡፡
4. በህግ ወይም በመመሪያ ከተፈቀደው ውጭ የውሃ አገልግሎቱን አላግባብ ሲጠቀም የተገኘ ደንበኛን ያሳወቀ እና እርምጃ እንዲወሰድ ያደረገ እና በቅርንጫፍ ጽ/ ቤቱ ሥራውን በሠሩት የሚመለከታቸው አካላት እና በበላይ ኃላፊዎች ውጤቱ ሲረጋገጥ በእያንዳንዱ ህገ ወጥ አጠቃቀም ጥቆማ ማበረታቻ የ 5 ደንበኞች የንባብ ክፍያ ተሰልቶ ለቆጣሪ አንባቢው በማህበሩ በኩል የሚከፈል ይሆናል፡፡
5. ከሶስት ወር በላይ የተጠቀመበትን ውሃ ሳይከፍል የሚጠቀም ደንበኛን በመጠቆም እና ቆጣሪው እንዲነሳ በማድረግ ውዝፉ ገቢ እንዲሆን በማድረግ ውጤት ያስገኘ ቆጣሪ አንባቢ በቅርንጫፍ ጽ/

ቤቱ የሚመለከታቸው አካላት ውጤቱ ሲረጋገጥ በእያንዳንዱ ቆጣሪ ማበረታቻ የ 10 ደንበኞች የንባብ ክፍያ ተሰልቶ ለቆጣሪ አንባቢው በማህበሩ በኩል የሚከፈል ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 16

## የቆጣሪ አንባቢዎች ለሚፈጽሙት ጥፋት ቅጣት

1. ባለስልጣኑ ከቆጣሪ ንባብ ሥራ ጋር በተያያዘ በሠራተኞች የህብረት ስምምነት የቅጣት ሰነድ ላይ የተቀመጠው የቅጣት ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ ለማህበራት የቆጣሪ አንባቢ ሠራተኞች የሚተገበር ይሆናል፡፡
2. የንባብ ፕሮግራሙን ለደንበኞች በግልጽ ሊነበብ በሚችል ማስታወቂያ በወረዳ ጽ/ ቤቶች ፣ በሸማቾች ማህበር ሱቆች ፣ ብዙ ሰው በሚሰበሰብበት የመንደር አደባባዮች በመለጠፍ ደንበኞች ፕሮግራማቸውን አውቀው እንዲጠብቁት ያላደረገ ቆጣሪ አንባቢና ማህበር ይህ አለመፈጸሙ በአንባቢ አስተባባሪዎች ሲረጋገጥ ወይም ደንበኞች ማስታወቂያ እንዳልተለጠፈ ሲያሳውቁና ሲረጋገጥ ወይም የወረዳ አስተዳደሩ ሲያሳውቅ ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጸመ ሲሆን ቆጣሪ አንባቢውና ማህበሩ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሰው ጥፋት በማንኛውም ማህበሩ የንባብ ስራ በሚሰራባቸው አካባቢዎች በድጋሚ ከተከሰተ ወይም ከተፈጠረ ከማህበሩ የወር ክፍያ ላይ የ 25 ውሎች ንባብ ሂሳብ ተሰልቶ በመቀነስ ለቅርንጫፍ ጽ/ ቤቱ ገቢ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ የተጠቀሰው ጥፋት በማንኛውም ማህበሩ የንባብ ስራ በሚሰራባቸው አካባቢዎች ለሶስተኛ ከተፈጠረ የማህበሩ ውል እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡
5. በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በአንድ ማህበር ውስጥ የሚሠሩ 5 አባለት ለማንኛውንም አይነት ቅጣት የተዳረጉ ከሆነ ማህበሩ ወይም ኢንተርፕራይዙ በስሩ ያሉ ሠራተኞችን ማስተዳደርና መምራት እንዳልቻለ ተቆጥሮ ውሉ ይሰረዛል፡፡
6. የቆጣሪ አንባቢው ማህበሩ በአባላቱ በኩል በቀጥታ እንዲፈፅማቸው ውል የገባባቸውን ውሃ ቆጣሪ ንባብ ሥራ ማለትም በየወሩ መነበብ ያለበትን ቆጣሪ በየወሩ ሳያነብ በግምት የሚያስተላልፍ እና የቆጣሪ ንባብን በካርድ ላይ በተገቢው ያልመዘገበ ቆጣሪ አንባቢ ጥፋቱ የተፈጸመው ከ 10 ባልበለጡ ደንበኞች ላይ ሲሆን የ 10 ደንበኞች የንባብ ክፍያ ተሰልቶ ከወር ደሞዙ በማህበሩ በኩል ይቀጣል ማህበሩም የገንዘብ ቅጣቱን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ያደርጋል ፡፡
7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ የተጠቀሱትን ጥፋቶች ከ 10 በላይ ደንበኞች ወይም ውል ቁጥሮች ላይ የፈጸመ ቆጣሪ አንባቢ ከሥራው ይታገዳል፡፡

8. በባለስልጣኑ ለደንበኞች እንዲበተን የሰጠውን ማስታወቂያ ፣ማስጠንቀቂያ እና የመሳሰሉትን ለደንበኞች ያላደረሰ ቆጣሪ አንባቢ ጥፋቱ ለመጀመሪያ ግዜ የተፈጸመ ሲሆን የ 5 ደንበኞች የንባብ ክፍያ ተሰልቶ ከወር ደሞዙ በማህበሩ በኩል ይቀጣል ፣ ማህበሩም የገንዘብ ቅጣቱን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ያደርጋል ፣ ማህበሩም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ ቆጣሪ አንባቢው ለሁለተኛ ጊዜ ድርጊቱን ከተፈጸመ ቆጣሪ አንባቢው ከንባብ ስራ ይሰናበታል፡፡ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተመሳሳይ ጥፋት በአንድ ወይም በተለያዩ አንባቢዎች ለሶስት ጊዜ በአንድ ማህበር አባላት ከተፈጸመ የማህበሩ ውል ይሰረዛል፡፡

9. የውሃ ቆጣሪ ዞሮ መገጠሙን እያወቀ ያላሳወቀ ወይም ከውሃ ደንበኞች ጋር በሁኔታው የተደራደረ ወይም በቀጥታ በህገ ወጥ ድርጊቱ የተሳተፈ ቆጣሪ አንባቢ ከሥራው ታግዶ በህግ የሚጠየቅ ይሆናል፡ ፡ ይህ ድርጊት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በአንድ ማህበር ውስጥ ከሶስት ሠራተኞች በላይ ተፈጽሞ ሲገኝ ሠራተኞቹን የቀጠረው ማህበር ውል ይሰረዛል ፣ ለተፈጠረውም ችግር በህግ አግባብ የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

10. በሚሰማራበት ክልል ህገ ወጥ ቅጥያ መፈጸሙን እያወቀ ሪፖርት ያላደረገ ወይም ህገ ወጥ ቅጥያ ከሚፈጽሙ ጋር ተባበረ ቆጣሪ አንባቢ ከሥራው ታግዶ በህግ የሚጠየቅ ይሆናል፡፡ ይህ ድርጊት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በአንድ ማህበር ውስጥ ከሶስት ሠራተኞች በላይ ተፈጽሞ ሲገኝ ሠራተኞቹን የቀጠረው ማህበር ውል ይሰረዛል ፣ ለተፈጠረውም ችግር በህግ አግባብ የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

11. በሚሠማራበት ክልል ( በድንገተኛ አደጋ ከሚያጋጥም ስብራት ውጪ ) የቆጣሪ አንባቢው በአካባቢው የቆጣሪ ንባብ ፕሮግራሙ ሆኖ ሳለ ከሁለት ቀን በላይ ያፈሰሰ የውሃ መስመር በህብረተሰቡ ጥቆማ ከተገኘ ለቆጣሪ አንባቢው ለማበረታቻ ሊከፈለው ከተመዘገበለት ማንኛውም ክፍያ ላይ ለእያንዳንዱ የሚያፈስ መስመር የ 2 ደንበኞች የንባብ ክፍያ ተሰልቶ ከወር ደሞዙ በማህበሩ በኩል ይቀጣል ማህበሩም የገንዘብ ቅጣቱን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ያደርጋል ፡፡

12. የውሃ ቆጣሪ አንባቢው በሚሠማራበት ክልል እርሱ በተመደበበት ጊዜ ውስጥ በውሃ መስመር ላይ ተፈጸመ ህገ ወጥ ግንባታ በህብረተሰቡ ጥቆማ ከተረጋገጠ ለቆጣሪ አንባቢው ለማበረታቻ ሊከፈለው ከተመዘገበለት ማንኛውም ክፍያ ላይ ለእያንዳንዱ ህገ ወጥ ግንባታ የ 2 ደንበኞች የንባብ ክፍያ ተሰልቶከወር ደሞዙ በማህበሩ በኩል ይቀጣል ማህበሩም የገንዘብ ቅጣቱን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ያደርጋል ፡፡

13. በሚሠማራበት ክልል እርሱ በተመደበበት ጊዜ ውስጥ ከአንድ ሳምንት የዘለለ የውሃ ስርጭት መቋረጥ ወይም በማንኛውም ጊዜ የተከሰተ የውሃ ብክለት ማጋጠሙን እያወቀ ሳያሳውቅ የቀረ ቆጣሪ አንባቢ ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲፈጸም ቅርንጫፍ ጽ/ ቤቱ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለማህበሩ ይሰጣል ፣

ማህበሩም ለቆጣሪ አንባቢው እንደሁኔታው ተገቢውን ቅጣት ወይም የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ቅርንጫፉ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡ ቆጣሪ አንባቢው ይህንን ጥፋት በድጋሚ ከፈፀመ ችግሩ በተፈጠረ ጊዜ በባለስልጣኑ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች እየተረጋገጠ ለማህበሩ ሲቀርብ የ 5 ደንበኞች የንባብ ክፍያ ተሰልቶ ከወር ደሞዙ የሚቆረጥበት ይሆናል ማህበሩም የገንዘብ ቅጣቱን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ያደርጋል ፣ በአንድ ዓመት ውስጥ ከሶስት ጊዜ በላይ ተደጋጋሚ ተመሳሳይ የማሳወቅ ችግር የፈፀመ ቆጣሪ አንባቢ ከባለስልጣኑ ጋር ተባባሪ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከሥራ ይታገዳል፡፡ በተመሳሳይ በአንድ አመት ግዜ ውስጥ ሶስት አባላት በተደጋጋሚ ( ከሁለት በላይ )ጥፋት ከፈፀሙ ማህበሩ ሠራተኞቹን መምራት እና መከታተል እንዳልቻለ ተቆጥሮ ውሉ ይቋረጣል፡፡

14. በማንኛውም ሁኔታ ከባለስልጣኑ ደንበኞች ጋር ጸብ የፈጠረ ፣ አግባብ ባልሆነ አቀራረብ ደንበኞችን ያጉላላ ፣ ከደንበኞች በማንኛውም ሁኔታ ገንዘብ የተቀበለ ፣ ከራሱ ወጪ ወደ ደንበኞች ጊቢ ሌላ ሰው ይዞ የገባ ቆጣሪ አንባቢ ከሥራው ይታገዳል፡፡ በተመሳሳይ በአንድ አመት ግዜ ውስጥ ሶስት አባላቱ ከላይ የተገለፀ ውን ጥፋት ከፈፀሙ ማህበሩ ሠራተኞቹን መምራት እና መከታተል እንዳልቻለ ተቆጥሮ ውሉ ይቋረጣል፡፡

15. በህግ ከተቀመጠው ውጪ ምክንያት በማቅረብ የውሃ ቆጣሪ ንባብ ሆን ብሎ ሳያነብ በመቅረት ደንበኞችን ያጉላላ እና የባለስልጣኑን ባጅ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ በደንበኞች በተጠየቀ ጊዜ መታወቂያውን ለማሳየት ፍቃደኛ ያልሆነ ቆጣሪ አንባቢ ጉዳዩ በማስረጃ ሲረጋገጥ ከሥራው ይሰናበታል፡፡ በተመሳሳይ በአንድ አመት ግዜ ውስጥ ሶስት አባላቱ ከላይ የተገለፀ ውን ጥፋት ከፈፀሙ ማህበሩ ሠራተኞቹን መምራት እና መከታተል እንዳልቻለ ተቆጥሮ ውሉ ይቋረጣል፡፡

## አንቀፅ 17

## ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ያልተወጣ የስራ መሪ ወይም ፈፃሚ፣ በስራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ወይም በህብረት ስምምነቱ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ አግባብ ባለው የሃገሪቱ ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 18

## መመሪያውን የማሳወቅ ግዴታ

የደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት የባለስልጣኑ የሥራ ሃላፊዎች፣ ሰራተኞች ፣ ከባለስልጣኑ ጋር የቆጣሪ ንባብ ስራ ለማከናወን ውል የገቡ ማህበራት ፣ደንበኞች እና የሚመለከታቸው አካላት ስለ አሰራሩ እና ስለመመሪያው አፈፃፀም በቂ እውቀት እንዲኖራቸው የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀፅ 19

## መመሪያውን ስለማሻሻል

ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማንኛውም ጊዜ መመሪያውን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## አንቀፅ 20

## የመተባበር ግዴታ

ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በየትኛውም ደረጃ ያሉ የባለስልጣኑ ኃላፊዎች፣ ሰራተኞች ፣ የሚመለከታቸው መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፣ ከባለስልጣኑ ጋር የቆጣሪ ንባብ ስራ ለማከናወን ውል የገቡ ማህበራት ወይም ህግና ደንብ እንዲያስከብሩ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት፣ ማንኛውም ሰው እና ደንበኞች የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 21

## ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎች ወይም አሰራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## አንቀፅ 22

## መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተፈርሞና የባለሥልጣኑ ማህተም ካረፈበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አወቀ ኃይለማርያም**

**የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን**

**ዋና ሥራ አስኪያጅ**